# አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት)
# UNITY FOR DEMOCRACY AND JUSTICE PARTY (UDJ)

## ከአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት)

## የተሠጠ መግለጫ

## ሕግን በመጣስና በወረደ ሥነ-ምግባር በመጠቀም

## አሸናፊነት አይገኝም!

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፖርቲ (አንድነት) በመጪው የ2002 ዓ.ም ምርጫ ጠንከራ ተፎካካሪ እንዳይሆን ለማድረግ ኢህአዴግ እየወሰዳቸው ያሉ ርምጃዎች ሕግን የሚጥሱና የወረደ የሥነ-መግባር ደረጃን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ሕግን በመጣስና በወረደ ሥነ-ምግባር በመጠቀም አሸናፊነት አይገኝም፡፡

የሕግ ጥሰቱና በወረደ ሥነ-ምግባር የመጠቀሙ የቅርብ ዓላማ ግልጽ ነው፡፡ አንድነት ከሕዝብ ጋር አንዳይገናኝና በህዝብ ጉዳይ ላይ እንዳይወያይ፣ ሕዝብ የአንድነትን አቋም እንዳያውቅና ያሉትን አማራጮች እንዳያመዛዝን ለማድረግና በዚህ ዓይነት ግርግር አሸናፊ ሆኖ ለመውጣት ነው፡፡ አንድነትም ሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚህ ዓይነት አካሄድ አይደናገሩም፡፡

በአሁኑ ጊዜ ኢህአዴግ አላማውን ለማሳካት የሚጠቀምባቸው ብልሹ ስልቶች ሦስት ናቸው፡፡ አንደኛው ስልት በየደረጃው የሚገኙ የአንድነት አባላትን በፈጠራ ክስና በሀሰት ምስክር ፍርድ ቤት በማቅረብ፣ በማጉላላት፣ በማስፈራራትና በማሰር የፖርቲ ሥራ እንዳይሠሩ ማድረግ ነው፡፡

ሁለተኛው ስልት የአንድነት አባላትን በጥቅም ለመግዛት በመሞከር አሊያም በዛቻና በማስፈራራት ፓርቲው የሰጣቸውን ድርጅታዊ ሥራ አንዳይሠሩ ማደናቀፍ ነው፡፡ ይህ ስልት ሁለት መልክ አለው፡፡ አንደኛው መልክ የአንድነት አባላትን ወደየወረዳው ጽ/ቤት  በመጥራት ከኢህአዴግ ጋር አንድ ሆነው እንዲሠሩ ማባበል አሊያም የአንድነትን ዓላማ ማራመድ እንዲያቆሙና አርፈው እንዲቀመጡ ይህን ካላደረጉና በአንድነት ስም የፖለቲካ እንቅስቃሴ ማድረግ ከቀጠሉ ለህይወታቸው የሚያሰጋ አደጋ እንደሚያጋጥማቸው ማስጠንቀቅ ነው፡፡ ሁለተኛው ተዛማጅ መልክ

ከፌደራል ደህንነት የመጣን ነን የሚሉ ስማቸውን ለመናገር ወይም መታወቂያቸውን ለማሳየት ፈቃደኛ ያልሆኑ ወይም ድፍረቱ የሌላቸው ግለሰቦች ወደየወረዳው እየሄዱ ከወረዳ ባለሥልጣናት ጋር በማበርና በወረዳ ሹማምንት ጠቋሚነት ንቁ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ የአንድነት አባላትን ወደየወረዳው ቢሮዎች በማስጠራት ወይም ወደ አረፉበት የሆቴል ክፍል በስልክ በመጥራት ቀደም ሲል በወረዳ ኃላፊዎች የተሰጡ ማባበያዎችን፣ ማስጠንቀቂያዎችንና ማስፈራሪያዎችን መሰንዘር ነው።

ሦስተኛው ስልት በሀገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች የሚከሰቱ የጐሳና የሃይማኖት ግጭቶች መንስኤዎችን በአንነድነት አባላት ላይ በማላከክና ተጠያቂ በማድረግ አሊያም በግንቦት ሰባትና በፀረ ሽብርተኝነት ስም ለክስና ለእስራት መዳረግ ነው። ኢህአደግ በከፋፍለህ ግዛው ፖሊሲው በዘረጋው የጐሳ ፖለቲካ ምክንያት ለሚነሱ ግጭቶች በሕዝብ ፍላጐት ላይ የተመሠረተ ትክክለኛ መፍትሄ በመሻት ፈንታ ግጭቶቹ ስውር የፖለቲካ ዓላማ ያላቸው ወገኖች የሚፈጥሯቸውና የሚቀሰቅሷቸው ናቸው በማለት ችግሩን በንፁሀን ዜጐች ላይ ማላከክ ከዚያም አልፎ በተለይ በአንድነት አባላት ላይ የፈጠራ ክስ በመመሥረትና ለእስራት በመዳረግ የድርጅቱን እንቅስቃሴ ማስናከል የተለመደ ስልት ሆኗል። ለማስረጃነት ጥቂቶቹን በሠንጠረዥ በአባሪነት ቀርበዋል።

ኢህአደግ ከላይ የተመለከቱትንና ወደፊትም የሚፈጥራቸው የማደከሚያ ስልቶች ከአሁን ጀምሮ እስከ መጪው ምርጫ ድረስ በዘመቻ መልክ ተግባራዊ ለማድረግና የአንድነትንና የሌሎች ሀቀኛ ተቃዋሚ ድርጅቶችን ጥረት ለማክሸፍ ቆርጦ ተነስቷል። ጥረቱ ግን አይሳካለትም። አንድነትና አጋሮቹ በመተባበር የሕዝቡን ትግል ለድል ያበቃሉ።

ኢህአዴግ ያሉት አማራጮች ሁለት ናቸው። አንደኛው የለየለት አምባገነን መሆንና የአምባገነኖችን ታሪካዊ መንገድ በመከተል ይህችን አገር የችግር አዘቅት ውስጥ መክተት ነው። ሁለተኛው የሕግ የበላይነት የሰፈነበት፣ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የሚከበሩበት፣ ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ የሚካሄድበት ሥርዓት እንዲመሠረት የመንግሥትነት ሚናውን በመወጣትና ለሕዝብ ፍላጐት በመገዛት የአገር ማዳን ትግሉ አካል መሆን ነው።

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት)

ሐምሌ 17 ቀን 2001 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# በአንድነትለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት)

## አባላት ላይ እየደረሱ ያሉ በደሎች

| ተቁ | በደሉ የተፈፀመበት አባል ሥም | በደሉ የተፈፀመበት ቀን | የበደሉ ዓይነት በአጭሩ | በደሉን የፈፀሙ ሰዎች ስምና የሥራ ኃላፊነት | ክልል | ዞን | ወረዳና ከተማ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የፓርቲው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት | | ጽ/ቤት እንደዘጋ ማድረግና ማስፈራራት በፎቶ ተደግፎ የቀረበ:: | 1. አቶ እንደገና አማረ የበአዴን ተወካይ<br>2. አቶ አለልኝ ነውጤ የወረዳ አስተዳዳሪ<br>3. አቶ ፈለቁ አዳነ የፖለሲ አዛዥ<br>4. አቶ ምንውዬለት የሚሊሺያ ተጠሪ:: | አማራ | ም/ጎጃም | ደባይ ጠላት ወረዳ |
| 2 | አቶ እንድሪስ ሰይድ የፓርቲው ሰብሳቢ | 29/08/2001 | እስር ተፈጽመበታል | 1. አቶ እንዲሪስ የፖሊስ አባልና ተባባሪው | አማራ | ደቡብ ወሎ | ተሁለደሬ ሀይቅ ከተማ |
| 3 | 1. አቶ ጌታሁን አብዱ<br>2. አቶ መኮንን አብዱ ቡሽራ<br>3. አቶ አብዱ ሰኢድ ሽምዬ<br>4. አቶ ሙባረክ ሰኢድ<br>5. አቶ ግርማ ተሾመ<br>6 አቶ አብዲ መሐመድ | 23/08/2001 | የተወካዮች ም/ቤት አባል ከሆኑት የተ/አቶ መኪን ሰኢድ ጋር ተገናኝታችኋል በሚል የወረዳው አስተዳደር ቢሮ በመጥራት ማስፈራራትና ማሰጠንቀቂያ መስጠት:: | 1. አቶ አሊ መሐመድ ዋና አስተዳዳሪ | አማራ | ደቡብ ወሎ | ወረባቦ ወረዳ ቢሰቲማ ከተማ |
| 4 | አቶ ሙሉጌታ ፈንታ በተከሩ አቶ መኪን ሰኢድ አመልካችነት ለሥራ የሄዱ የደሴ ቅርንጫፍ የኢሠመጉ ኃላፊ | 24/09/2001 | በስም የተጠቀሱት የኢሠመጉ ኃላፊ በእኛ ፓርቲ አባል አመልካችነት ለማጣራት በመሄዳቸው ከወረዳው የፀጥታ ዘርፍ ኃላፊ ኪስ 200 ብር ሲሠርቁ ተገኝተዋል የሚል ክስ በመመሥረት 8 ወር የተፈረደባቸው:: | 1. አቶ አሊ መሐመድ ሰማኝ ዋና አስተዳደሪ<br>2. አቶ መኮንን ሁሴን ደመኔ ም/ፀጥታ ኃላፊ<br>3. አቶ ካሳሁን ደምሴ<br>4. አቶ ከበደ ሞሔ የጥቃቅን እና አነስተኛ ንግድ ጽ/ቤት ኃላፊ:: | አማራ | ደቡብ ወሎ | ወረባቦ ወረዳ ቢስቲማ ከተማ |
| 5 | አቶ አለሙ አባይነህ የፓርቲው ሰብሳቢ | 09/10/2001 | በፈጠራ ክስ በሬ ሠርቀሀል በማለት 4 አመት የተፈረደበት:: | | አማራ | ደቡብ ወሎ | ወረባቦ ወረዳ ቢስቲማ ከተማ |
| 6 | 1. አቶ አብዱ ሰኢድ አመዴ<br>2. አቶ አብዲ መሐመድ | ሐምሌ ወር 2001 | በሌሊት ስማቸው ባልታወቀ የወረዳ ታጣቂዎች እየደበደቡ ወደ ወረዳው ፖሊስ በመውሰድ ለ9 ቀናት ካሠሩ በኋላ በብር 1000 ዋስትና ተለቀዋል:: | | አማራ | ደቡብ ወሎ | ወረባቦ ወረዳ ቢስቲማ ከተማ |
| 7 | አቶ ማስረሻ የፓርቲው ሥራ አስፈፃሚ አባል | 28/10/2001 | በሀይማኖት ሽፋን ፖለቲካ ታራምደለህ በሚል የፈጠራ ክስ ተመስርቶባቸው ለእስር የተዳርገው በ4.000 ብር ዋስ የተፈቱ:: | ኢንስፔክተር ሲሣይ ከክልል የመጣሁኝ ነኝ የሚሉ | አማራ | ደቡብ ወሎ | ደሴ |

# በአንድነትለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት)

## አባላት ላይ እየደረሱ ያሉ በደሎች

| ተቁ | በደሉ የተፈፀመበት አባል ሥምና ጽ/ቤት | በደሉ የተፈፀመበት ቀን | የበደሉ ዓይነት በአጭሩ | በደሉን የፈፀሙ ሰዎች ስምና የሥራ ኃላፊነት | ክልል | ዞን | ወረዳና ከተማ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቡሌ ሆራ ጽ/ቤት | 13/06/2001 | በፓርቲው (የፓርቲያችን) ባንዲራውን በማውረድ የፓርቲውን ታፔላንም ነቅለው ወደ ከተማ ፖሊስ ጽ/ቤት ወስደው አስቀምጠዋል፡፡ | ፊታቸው በጨርቅ የሸፈኑ ታጣቂዎች፡፡ | | | ቡሌ ሆራ ወረዳ ሀገረማሪያም ከተማ |
| 2 | 1. አቶ ወርቁ አለምቦ የፓርቲው ጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴ ፀኃፊ የሆኑት<br>2. አቶ አወቀ ወልዴን | 16/06/2001 | 1. በፓርቲው ውስጥ ማንኛውንም የፖለቲካ ቅስቀሳ (ገለፃ) እንዳያደርጉ ማስፈራራት እንዲሁም ቢሮውን በማንአለብኝነት መዝጋት ፡፡<br>2. የፓርቲው ፀኃፊ አቶ አወቀ ወልዴን በእለተ ትንሣኤ ለ4 ቀን ማሰር፡፡<br>3. የፓርቲው ሰብሳቢ አቶ ወርቁ አለምቦን እንዲታሰር ማድረግ፡፡ | 1. አቶ ተስፋዬ ታዬ የወረዳው ካድሬ<br>2. ወ/ር ታረቀኝ መላኩ ካድሬ ፡፡<br>3. ወ/ር ረባሼ ጁር<br>4. አቶ ተራማጅ ተፈራ የፖሊሲ አዛዥ፡፡ | | | አማሮ ለዩ ወረዳ |
| 3 | 1. አቶ ለማጎዳና ሰብሳቢ<br>2. አቶ ዳንኤል አዳማን ም/ሰብሳቢ<br>3. አቶ ታምራት ጋሞ ፀኃፊ | በ06/06/2001 | ለአንድ ሣምንት ሦስቱም እንዲታሠሩ ተደርገዋል፡፡ የፓርቲው ጽ/ቤትን እንዲዘጉ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአቸው ባለመፈፀማቸው፡፡ | 1. መ/አ ብሩክ ጨጋ የፖሊስ አዛዥ | | ጋሞ ጎፋ | ሣውላ |
| 4 | 6 የአመራር አባሎቻችን | | 6ቱም ፖሊስ ጣቢያ አፍሶ በመውሰድ 5ቱ ለ3 ቀን 1 አመራር ለ5 ቀን ታስረዋል፡፡ | | | ሲዳማ | ጭሬ ወረዳ |
| 5 | አቶ መሰና መኩሪያ | የእርሻ ማሣ ላይ የተተከለ ቀርቀሃ፤ አትክል አትክትልና ሰብል በእጅ በመማስና በመጨበመጨፍጨፍ ማውደም፡፡ ያችን አባልና አባልና ባለቤቱን በቃል፤ ሙሣሪያ አስፈራ አስፈራርተዋል፡፡ | 1. አቶ ባህሩ ወልዴ ጊዮርጊስ የፍትሕና የፀጥታ ኃላፊ፡፡<br>2. አቶ እስራኤል ባይጋ የወረዳው ሥራ አስፈፃሚ፡፡<br>3. አቶ ተሰማ በድሩ የጨልሻ ቀበሌ ሊ/መንበር፡፡ | | | ማረቃ ወረዳ | |
| 6 | አቶ ጌታቸው ኮይራ አሰከን የፓርቲው አመራር | በ14/07/2001 | የንግድ ተቋማቸው (ፋርማሲን) መዘዝጋት<br>እንዲለቅ ማስፈራራት፡፡ | የወረዳው ከፍተኛ አመራሮች | ደቡብ | ገሞ | ቁጫ ወረዳ |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 7 | የአንድነት ፓርቲ | 12/05/2001 | ፓርቲው በወላይታ ዞን በዳሞት ጋሌ ወረዳ የከፈተው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እስከአሁን መዘጋትና ታፔላ ነቅሎ መጣል | የወረዳው 9 የሚሆኑ አመራሮች በአንድነት | ደቡብ | ወላይታ | ዳሞት ጋሌ ወረዳ ቦዲቲ ከተማ |